**ይድረስ ለኦቦ ሌንጮ ለታ!**
**ከጌታሁን ሄራሞ**

ጅምር የትምህርት ዳራቸው ኬሚካል ምህንድስና ነው፤ ይበልጥ የሚታወቁት ግን በፖለቲካው ዓለም ተሳትፎአቸው ነው፡- ቀደም ሲል የኦነግ ከፍተኛ አመራር ነበሩ፤ ቀጥሎም ከኦነግ ጋር ፍቺ ፈፅመው የኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ግንባር መስርተው ሊቀመንበር ሆኑ፤ በአሁኑ ወቅትም በጠ/ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ የተደረገውን ጥሪ ተቀብለው ወደ ሀገር ቤት ከመግባታቸውም ባለፈ ፓርቲያቸው ኦዴግ ከኦዴፓ ጋር ለመዋሀድ በቅቷል፡-....ኦቦ ሌንጮ ለታ።

ታዲያ ኦቦ ሌንጮ በእንግሊዘኛው “The origin of Ethnic politics in Ethiopia” በሚል ርዕስ የፃፉት መጣጥፍ ሰሞኑን በማሕበራዊው ሚዲያዎች ለንባብ በቅቶ ሲንሸራሸር ነበር። የፅሑፉ ሀሳብ በአጭሩ ሲጨመቅ፡- የኢትዮጵያ የብሔር ፖለቲካ በኢሕአዴግ በጎ ፈቃድ የመጣ አይደለም፤እውነተኛ ምንጩም ሆነ ሰበቡ ካለፈው የሀገሪቱ የፖለቲካ ታሪክ ጋር የተቆራኘ ነው....የሚል ነው። ኦቦ ሌንጮ ያለፈው ታሪክ በወቅቱ የታሪክ አቅጣጫ ላይ ስለሚያሳድረው ተፅዕኖ ለማስረዳት የተጠቀሙት የዕውቁን ካርል ማርክስ አባባልን ነው፤ማርክስ የሚለው እንደዚህ ነው፡- “Men make their own history, but they do not make it as they please, they do not make it under self-selected circumstances, but under circumstances existing already, given and transmitted from the past." ይህ የማርክስ ትንታኔ ግልጽ ነው፤ ማርክስ ያለፈው ታሪክ በነባራዊው ሁኔታ ላይ አሻራውን እንደሚያሳርፍ ይጠቁምና ይህም የተወረሰው ታሪክ የሰው ልጆች ያሰቡትንና ያቀዱትን ሁሉ እንዳይፈፅሙ ማናቆ ሆኖ ያግዳቸዋል ይለናል። ስለዚህም የሰው ልጆች ስኬታማ በሆነ መልኩ ለውጥን ማምጣት ከፈለጉ ያለፈውን ታሪክ ማወቅ እንዳለባቸው ያስገነዝበል።

ታዲያ ከሀገራችን ፖለቲካዊ አውድ አኳያ ለዛሬው የኢትዮጵያ የብሔር ፖለቲካ መናኘት ሰበብ የሆነው የታሪካችን አካል የትኛው ይሆን? ኦቦ ሌንጮ የኋሊት ይወስዱናል...ወደ 1933 ዓ.ም...እ.ኤ.አ። ያኔ የወቅቱ የትምህርት ሚኒስቴር አቶ ሳሣሉ ፀዳሉ ከአንድ ምሁር የማይጠበቅ ፕሮፖዛል ለመንግስት አቅርበው ነበር...በቃ ሀገሪቱ ውስጥ ያሉ ቋንቋዎች በሙሉ ተደምስሰው አማርኛና ግዕዝ ብቻ ህልውናቸው እንዲጠበቅ የቀረበ ምክረ ሀሳብ! የቋንቋ Genocide! እንዴት ይደምሰሱ? ለሚለው ጥያቄ ሰውዬው እራሳቸው ምላሽ የሚኖራቸው አይመስለኝም። በእኔ ዕይታ የአቶ ሳሣሉ አስተሳሳብ ለውይይት እንኳን መቅረብ የሌለበት ነው፤ ለማንኛውም አቶ ሳሣሉ ያሉት እንደዚህ ነበር፡-

"ያገር ጉልበት አንድነት ነው፤አንድነትንም የሚወልደው ቋንቋ፣ልማድና ሃይማኖት ነው...በመላ ኢትዮጵያ ግዛት ለሥጋዊና ለመንፈሳዊ ሥራ ያማሪኛና የግዕዝ ቋንቋ ብቻ በሕግ ፀንተው እንዲኖሩ ሌላው ማናቸውም የአረማያን ቋንቋ ሁሉ እንዲደመሰስ ማድረግ ያስፈልጋል።"

እንግዲህ ኦቦ ሌንጮ የማርክስን አባባል ከአቶ ሳሣሉ..."አማርኛ-ግዕዝ" ብቻ...ምክረ ሐሳብ ጋር እያዋዙ ለዛሬው የብሔር ፖለቲካ መፀነስ ሥር መሠረቱ ያኔ እንደተጣለ ያብራሩልናል። ወያኔ/ኢሕአዴግም የዚህ ዕድሜ ጠገብ የብሔር ፖለቲካ ወራሽ እንጂ ፈጣሪ እንዳልሆነ ይነግሩናል። ከዚህም ጋር አያይዘው የኢትዮጵያ የብሔር ማንነት ጥያቄ ምንጩ ፖለቲካ መሆኑን ይጠቁማሉ...ፅሑፋቸው ውስጥ በተደጋጋሚ "Politicization of Ethnicity" የሚለውን ቃል ይጠቀማሉ። እናም ኦቦ ሌንጮ ኢትዮጵያ ውስጥ ለተስተዋለው የብሔር ፖለቲካ ንፋስ ኢሕአዴግ መመስገንም ሆነ መነቀፍ የለበትም ይላሉ፤ ነቀፌታውም ሆነ ሙገሳው መጉረፍ ያለበት ወዳለፈው ታሪክ ነው።
በግርድፉ ስንመለከተው ይህ የኦቦ ሌንጮ ለታ መደምደሚያ ትክክል ይመስላል፤ሆኖም ግን በእኔ እምነት የታሪክ ቤት መስኮቶች አያሌ ሆነው ሳሉ ኦቦ ሌንጮ ለታ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ክስተቶችን በአንዱ መስኮት ብቻ ለማየት የመረጡ ይመስላል።

ኦቦ ሌንጮ የኢትዮጵያን የብሔር ፖለቲካ ምንጭን ለማፈላለግ ጥቅም ላይ ያዋሉት ፅንሰ ሐሳብ በእንግሊዘኛው "Historicism" ተብሎ የሚጠራው ነው። ለጊዜው አቻ የአማርኛ ቃል ያላገኘሁለት ይህ ፅንሰ ሐሳብ በሰው ልጆች የወደ

ፊት ዕጣ ላይ ያለፈው ታሪክ የሚኖረው ጫና ወሳኝነት እንዳለው የሚያትት ነው። ስለዚህም የዚህ ፅንሰ ሐሳብ አራማጆች ትልቁ የሌት ተቀን ጥረታቸው በታሪክ መድረክ ላይ የተከሰቱትን ተዋንያንን በመመርመርና ትርጉም በመስጠት የታሪክ ዕድገትን ሕጎችን(Laws of Historical Developments) ማሰስ ነው። ይህ የታሪክ ምርምር ስኬታማ በሆነ መልክ ከተጠናቀቀ፤ የወደ ፊቱን የታሪክ ዕድገት አቅጣጫን ሕጎቹን ተጠቅሞ መተንበይ ቀላል ይሆናል። በሂደቱም የፍልስፍናው ተከታዮች ታሪክን ተንተርሰው ፖለቲከኞች ሊከተሉት ዘንድ የሚገባውን አቅጣጫን ለማመላከት ጥረት ያደርጋሉ። የ"Historicism" ቀኖና በእንግሊዘኛ በአጭሩ ሲቀመጥ ይህን ይመስላል፦ "History is Controlled by specific historical or evolutionary laws whose discovery would enable us to prophesy the destiny of man."

ጀርመናዊውና ዕውቁ የሶሻሊስት ርዕዮተ ዓለም ፊታውራሪ የነበረው ካርል ማርክስ የ"Historicism" ፅንሰ ሐሳብ አራማጅ ነበር፤ የካርል ማርክስ የ"Historicism" ንድፈ ሀሳብ ሥሩ ሲፈተሽ ወደ ግሪኩ ፈላስፋ ሄራክሊቶስ፤ ፕሌቶና ሄግል ድረስ ይወስደናል።

ወደ ኦቦ ሌንጮ ፅሑፍ ልመልሳችሁ ነው፤ ፀሐፊው በጠቀሱት የካርል ማርክስ አባባል ውስጥ የሰው ልጆች ለማሕበረሰብ ዕድገት አያሌ ሕልምና ራዕይ ቢኖራቸውም ይኼው ሕልማቸው ካለፈው ታሪክ ጋር ጥምረት ከሌለው ጥረታቸውና ድካማቸው ሁሉ ከንቱ ልፋት ይሆናል የሚል ሀሳብ ሰፍሯል። ስለዚህም ነባሩ ትውልድ እንቅስቃሴውንና ትልሙን ሁሉ መቃኘት ያለበት ባለፈው ታሪክ አስታክኮ መሆን አለበት ...under circumstances existing already, given and transmitted from the past. ስለዚህም በኦቦ ሌንጮ ምልከታ መሠረት ቀደም ሲል በነበረው የኢትዮጵያ ፖለቲካ የብሔር ጭቆና መኖሩ ለወያኔ-ኢሕአዴግ የብሔር ፖሎቲካ አስገዳጅ ሁኔታ ነበር...Note that, here, TPLF/EPRDF was only a passive force (for Obbo Leencho) to be guided by the circumstances transmitted from the Past!

ኦቦ ሌንጮ ለታ በእኔ ምልከታ በፅሑፋቸው ውስጥ ሁለት ግዙፍ ሕፀፆችን ፈፅመዋል፤ እነርሱም፦

**1. መጣጥፉ ሚዛናዊናት ይጎድለዋል!**

የአንድ መጣጥፍ ይዘትና ብስለት ከሚለካባቸው መስፈርቶች አንዱና ዋነኛው ፀሐፊው ከሚደግፈው አመለካከት ውጪ ያሉትን ተፎካካሪና ተቃርኖአዊ ፅንፎችን ለአንባቢያን ይፋ በማድረግ ብቃቱ ነው። ማለትም ፀሐፊው ከያዘው አቋም በታቀራኒው ረድፍ የቆሙትንም ዕይታዎች ወደ መድረክ ማምጣትና ለታዳሚው የራሱ ዕይታ ከሌሎች ተፎካካሪ ፅንሰ ሐሳቦች ነጥሮ የወጣበትን አመክንዮአዊ መሠረቱን ማስረዳት ይጠበቅበታል። ለምሳሌ ሊብራል ዲሞክራሲን የሚደግፍ ፀሐፊ ስለ “Authoritarianism” ፅንፍም ሊል ዘንድ የሚገባው ነገር መኖር አለበት። ስለ አሐዳዊው ሀገረ-መንግስት አወቃቀር ሽንጡን ገትሮ የሚከራከር ተሟጋች ፌዴራላዊ የሚባል አወቃቀር እንዳለም ለታዳሚው ጠቁሞ የራሱ አቋም ከፌዴራሊዚሙ በምን መስፈርት እንደሚሻል ማስረዳት ካልቻለና አንዱን ጽንፍ ብቻ አነብንቦ ከመድረክ ከወረደ የፅሁፉ ሚዛናዊነት መቀመቅ እንደወረደ ይቆጠራል...Just to say that a writer must display all contrasting views on the stage and convince why his view is more preferable, more convincing.

በአንድ ፅንሰ ሐሳብ ዙሪያ የትየለሌ ዓይነት ተነፃፃሪ ዕይታዎች እያሉ፤ “አንድ ለእናቱ” ዓይነት አቋማቸውን ብቻ አንፀባርቀው እንደ ዋዛ ከመድረክ የሚወርዱ ፖሎቲከኞች ምክንያታቸው ከሁለት አንዱ ነው፦ የመጀመሪያው በአንፃራዊ የፖለቲካ ዕውቀት ዘርፍ...Comparative Political knowelege...ያላቸው ግንዛቤ አነስተኛ መሆኑ ነው። አንዳንድ ሰው አስቀድሞ የያዘውን አስተሳሰብ ላለመልቀቅ ብቻ ሲል በሌላ ፅንፍና ጎራ ያሉትን አመለካካቶች ከመቃኘት ራሱን ያቅባል፤ በነገራችን ላይ ይህ ዕቀባ በራስ የአለመተማማን ምልክት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ሁሌም በራሳቸው አስተሳሳብ ዛቢያ ብቻ የሚሽከረከሩ ሰዎች የንባብ ውሎአቸውም ሆነ አዳራቸው ተመሳሳይ የሐሳብ ፍሰቶች ባሉበት ሰፈር ነው። ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ የአንባቢን የንባብ አቅምም ሆነ ንቃተ ሕሊና አሳንሶ

ከመገመት ጋር የተያያዘ ነው(Audience Undermining)። በዚህኛው ምድብ ያሉ ፀሐፍት እነርሱ ከያዙት አቋም በተቃራኒ ሌሎች ተፎካካሪ አተያዮች እንዳሉ ድብን አድርገው ያውቃሉ፤ ነገር ግን ይህ በእነርሱ ዘንድ ያለው መረጃ አንባቢ ዘንድ የሌለ ስለሚመስላቸው ልድገምና "አንድ ለእናቱ" ዓይነት ምልከታቸውን ዘርግፈው ውልቅ ይላሉ።

ለኦቦ ሌንጮ "Historicism" ብቸኛ ታሪክን መፈተሻ መሣርያ ነው። ነገር ግን እነ ማርክስ ይህን ፅንሰ ሐሳብ እንደ ቀኖና ባዋቀሩበት ማግስት የተቃወሙአቸው አያሌ ፈላስፎች ነበሩ። ከነዚህም ውስጥ አንዱ ካርል ፖፐር( karl Popper) ነው(ከላይ ስለ "Historicism" የሰጡሁትን ገለፃ የተጠቀምኩት ከዚሁ ፈላስፋ ተውሼ ነው)። በትውልድ አውስትሪያዊ ሆኖ በዜግነቱ ግን እንግሊዛዊ የሆነው ይህ ፈላስፋ ከፍልስፍናው በሻገር በተፈጥሮ ሳይንሱም የገዘፈ ዕውቀት የነበረው የ20ኛው ክፍለ ዘመን ሊቅ ነው። ፖፐር የማርክስን "Historicism" በፅኑ ካሄሰበት ሥራዎቹ ውስጥ ሁለት መፅሐፍት ተጠቃሽ ናቸው። የመጀመሪያው እ.ኤ.አ በ1957 የተፃፈው "The Poverty of Historicism" የተሰኘው መፅሐፉ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ እ.ኤ.አ በ1962 የተፃፋው "The Open Societies and its Enemies" መፅሐፉ ነው። በሁለቱም መፅሐፎቹ ፖፐር የማርክስ "Historicism" ከሂራክሊቶስም ሆነ ከሄግል "Historicism" የከፋ አደገኛ ፍልስፍና ነው ሲል አውግዟል። የውግዘቱ መንስኤ ምን ይሆን?

በፖፐር ዕይታ በታሪክ ውስጥ የሚንፀባረቅ አንድ ሁነት በየትኛውም መልኩ ሕግ መሆን አይችልም። ይህን በተመለከተ ፖፐር እንደዚህ ይላል፦ "The evolution of life on earth , or of human society , is a unique historical process …its description however, is not a law, but only a singular historical statement…Study of history may reveal trends. However, there is no guarantee that these trends will continue. In other words, they are not laws"

ፖፐር እያለን ያለው… በታሪክ ሁነት በአንድ የጊዜ አንጓ ውስጥ የተፈጸሙትን ክስተቶች እየመዘዝን ሕግ ማድረግ የሚታሰብ አይደለም፤ እነዘህ ክስተቶች አዝማሚያዎች(Trends) እንጂ ሕጎች አይደሉም:: ሕግና አዝማሚያ ደግሞ ለየቅል ናቸው፤ ለምሳሌ የመሬት ስበት ሳይንሳዊ ሕግ ነው፤ የስበት ሕጉ መሬት ላይ እስካለን በአንድ የጊዜ ቋት ውስጥ ታይቶ ሊጠፋ የሚችል አዝማሚያ አይደለም። አዝማሚያዎች ጊዜና ቦታን እየለዋወጡ ሊከስሙ ወይንም ዳግም ሊከሰቱ ይችላሉ፤ ይህ የአዝማሚያ ጊዜአዊነትም ወይም ዳግም መመለስ በፋሽን እንዱስትሪው በስፋት ይታወቃል። ዛሬ ፋሽን የሆነው የልብስ ቀለም ነገ ምን ሊሆን እንደሚችል አስረግጥ የሚነግረን ሕግ የለም። ግምቶች ግን ሊኖሩ ይችላሉ….Hence that is why there is color forecasting profession and not color prophesying discipline.

ለካርል ፖፐር በማሕበራዊውና ፖለቲካዊው ተሳትፎ የሰው ልጆችን ባሕርይ መገመት እጅግ አዳጋች ነው፤ ታሪክ ደግሞ የሚከወነው በነዚሁ ለመገመት እጅግ አዳጋች ባሕርይን ባነገቡ ልህቃን ነው። ካርል ማርክስ ያለፈውን የሰው ልጆች የታሪክ ሂደቶች አጥንቶ ህጎችን አዋቀረ፤ በነዚህ ሕጎች ላይ ተመስርቶም የሰው ልጆችን ፍጻሜ…destiny…እርግጠኛ ሆኖ ተነበየ..ኮሚኒዝም ልንደርስበት ዘንድ የሚገባ ግባችን ነው በማለት!

አዝማሚያን እንደ ብረት የጠነከረ ሕግ(Iron Laws) ከቆጠርን ልግምተኝነትን(Passiveness) ይሰለጥንብናል፤ የካርል ፖፐር አንዱም የ"Historicism" ተቃውሞው ጽንሰሀሳቡ የሰው ልጆች ወቅታዊውን የዕውቀት እርከናቸውን ተጠቅመው መፍትሔ ሊያመጡበት የሚችሉበትን ክህሎት ያለዝባል የሚል ነው፤ For him, historicism is anti activism. አንድ ሰው የዚህ የ"Historicism" ፍልስፍና ተከታይ ከሆነ ሁሉንም የዛሬ ሁነቶች የሚቃኘው ትናንት በተፈፀመው ታሪክ ውስጥ ሆኖ ነው። ከዛሬው ዕድገት፤ሥልጠኔና አስተሳሰብ ጋር መሄድ እጅግ ያቅተዋል…Passivity reigns and activism dies in the minds of historicists.

ኦቦ ሌንጮ ምስጋና ይግባቸውና ኢሕአዴጋዊን አልፎ ተርፎም የኢትዮጵያ የብሄር ፖለትከኞች ማርክሳዊያን "Historicists" መሆናቸውን ይፋ አድርገውልናል። ለካስ ለዚህ ነው መቶ ዓመታትን ወደ ኋላ እየመለሱን በትናንት ታሪክ ውስጥ ብቻ ሊያኖሩን ደፋ ቀና የሚሉት…በትናንት ታሪክ ሊመሩን የሚከጅሉት…በአንድ የታሪክ ምዕራፍ ውስጥ የተከሰቱትን ስሕተቶች እንደ አዝማሚያ ከመቁጠር ይልቅ እንደ ሕግ በመያዝ ወቅቱን የሚመጥን መፍትሔ

ከማፈላለግ ይልቅ "አንድ ለእናቱ" ዓይነት መፍትሔን ብቻ የሚያንፀባርቁት። ኦቦ ሌንጮ እኮ በግልፅ አስቀምጠዋል...የብሔርን ፖለቲካ የወለደው ወያኔ/ ኢሕአዴግ አይደለም፤የትናንት ታሪክ ያወረሰን ጣጣ ነው ብለውናል። እሺ ከትናንት የወረስናው ጣጣ ይሁን...ግን ለዚህ ጣጣ የመፍትሔው አቅጣጫ አንድና አንድ ብቻ ነው?... በነ አቶ ሳሃሉ ፀዳሉ ትንኮሳ ላይ ተመስርተን የብሔር ፖለቲካን እስከወዲያኛው ማጦዝ!! በዓለም ደረጃ ታይቶ የማይታወቀውንና ከነአካቴው መገንጠልን የሚፈቅድ የቋንቋና የብሔር ፌዴራሊዚም ሀገሪቱ ላይ ማስፈን!! በቃ ለነ ኦቦ ሌንጮ ከዚህ ውጪ ሀገሪቱን የሚታደግ ሌላ መላ የለም... They are so sure about it...They can prophesy about it clearly and boldly because they endorse historicism...በቅርቡም ኦቦ ሌንጮ ለታ የብሔር ፌዴራሊዝም ከተወገደ በሀገሪቱ ውስጥ የደም መፋሰስ ዕውን ይሆናል በማለት ሊያስፈራሩን የሞከሩትን እዚህ ጋ ማንሳት ይቻላል። ለእነርሱ የብሔር ፖለ ካ እንደ ፋርስና ሜዶን ህግ ለድርድር የማይቀርብ የማይነቀናቅ ብረት-ለበስ፤ ስሕተት-አልባ ህግ ነው!

አፈሩ ይቅለላቸውና አቶ መለስ ዜናዊም በስልጣን ዘመናቸው ማግስት እንደ አንድ "Historicist" ያለፈውን ታሪክ ተንተርሰው ያዋቀሩት የብሔር ፌዴራሊዝም ለሀገሪቱ ዕድሜ ጠገብ እንቆቅልሽ ብቸኛ ፍቱን መድሃኒት ነው በማለት ጮቤ ረግጠው ነበር...የብሔር ፌዴራሊዚሙ ኢትዮጵያን ያፋራርስታል ብላችሁ የወቀሳችሁት በሙሉ እፈሩ፤ እንዲያውም የብሔር ፌዴራሊዝም ርዕዮታችን ሀገሪቱን ወደ አንድነት ጎዳና እያመጣት ነው...ወደሚል መደሚደሚያ ቢጤም ደርሰው ነበር።ሆኖም ግን ዛሬ ከቅድመ ኢሕአዴግ በፊት በገዥው መደብ ተንጸባርቆ ለነበረው የብሔር ጭቆና ቋንቋንና ብሔርን መሠረት ያደረገው ፌዴራሊዝም ብቸኛው መፍትሔ ያለመሆኑን መረዳት ያን ያህል አዳጋች አይደለም። የሚገርመው ሰሚ ጆሮ አጡ እንጂ አቶ መለስ የብሔር ፌዴራሊዝምን ባዋቀሩበት ማግስት የተቃወሙ እያሌ ዓለም አቀፍ ምሁራን ነበሩ፤ለዚህም ከዛሬ 20 ዓመታት በፊት በ"William Safran" እና "Ramon Maiz" አዘጋጅነት "Identity and Territorial Autonomy in Plural Societies" በሚለው ርዕስ ታትሞ ለንባብ የበቃውን መፅሐፍ በዋቢነት መጥቀስ ይቻላል። በመፅሐፉ ውስጥ በተለይም ሁለት የፖለቲካ ሳይንስ ምሁራን (Shaheen Mozaffar James R. Scarritt) የኢትዮጵያን የብሔር ፌዴራሊዝምንና የክልል አወሳሰንን ወደ ፊት ሊያስከትላቸው ከሚችላቸው መዘዞች ጋር አመሳክረው ተቃውመው ነበር።

ከዚህም ባለፈ...ትናንት በተቀደደው የታሪክ ቦይ እየፈሰሱ የብሔር ፌዴራሊዝምን ማጧጧፍ የሀገሪቱን አንድነት ለማቆየት ብቸኛው መፍትሔ ነው... በማለት ኦቦ ሌንጮ ያሰመሩት ሐሳብ በራሱ ፍተሻ የሚያስፈልገው ነው። በአሁኑ ወቅት የፌዴራሊዝም ምሁራን በጥናት ያረጋገጡት እውነት የሚለው ከዚህ ተቃራኒ ነው። እያሌ ብሔር ብሔረሰቦች ባሉበት ሀገር ቋንቋንና ብሄርን መሠረት ያደረገና የራስ ገዝ ሙብትን ያጎነፀፈ ፌዴራሊዝም የማታ ማታ ሀገሪቱን ሊበታትነት እንደሚችል የሚጠቁሙ ብዙ ጥናቶች አሉ። ለዚህም በፌዴራሊዝም በተለይም በብሔር ፌዴራሊዝም ተቃርኖአዊ ውጤቶች ዙሪያ ዶ/ር ሰሚር አሚን በቅርቡ በጠ/ሚኒስትር ፅ/ቤት ያቀረቡትን ትንታኔ በዋቢነት መጥቀስ ይቻላል። ፡ሰፋ ባለ መልኩ በዚህ ዙሪያ በቂ ግንዛቤ ለመጨበጥ ለምትፈልጉ ከዚህ በፊት በሌላ ፅሑፌ የጠቆምኩትን ምርጥ መፅሐፍ እንደገና ላስታውሳችሁ፡- "The Paradox of Federalism: Does self-Rule Accommodate or Exacerbate Ethnic Divisions? Edited by Jan Erk nad Lawerence M. Andeson.

እናም ኦቦ ሌንጮ ታሪካዊ አዝማሚያዎችን እንደ ሕግ በመቁጠር የመፍትሔውም አቅጣጫ አንድና አንድ ብቻ ነው ከሚልና ከነ ካርል ፖፐር ባለፈ በብዙ የወቅቱ የፖለቲካ ምሁራንም ዘንድ ውድቅ በሆነው ማርክሳዊ አስተሳሰብ ዛሬም ድረስ መቃኘታቸው ዘይገርም ነው። የትናንት ታሪክ በዛሬ ማንነት ላይ የሚጥለው አሻራ ባይካድም የሰው ልጆች ወቅታዊውን ሥልጣኔና ዕውቀት በመጠቀም የታሪክ አዝማሚያዎችን የመቀየር ዕምቅ አቅም እንዳላቸው መካድ የለብንም። የሚገርመው ኦቦ ሌንጮ በፅሑፋቸው በኢትዮጵያ አውድ የብሔር ፖለቲካን የወለደው ያለፈው የገዥ መደብ ፖለቲካ እንደሆነም በግልጽ በማስቀመጥ የወያኔ-ኢሕአዴግን መስመር የሚፃረር ሐሳብ መሰንዘራቸውን እዚህ ጋ ሳልጠቁም አላልፍም። ከላይ የጠቀስኩት የፖለቲካ ሳይንስ ፕሮፌሰሩ "Shaheen Mozaffar"ም ፖለቲካ ለብሔር ማንነት ቅርፅ እንደሚሰጥ ያምናል፤ ከዚህም አልፎ ፖለቲካ ብሔርን እስከመፍጠር ሁሉ ሊዘልቅ ይችላል ይለናል፡- "Politics moulds and sometimes creates ethnopolitical identity and animates its mobilization as a

strategic resource to organize collective action" የሀገራችን ዕውቁ ምሁር ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌም የወያኔ ብሔር ፖለቲካ የልህቃኑ እንደሆነ ካስገነዘቡን ሰነባብቷል። ኦቦ ሌንጮም ያረጋገጡልን ይህንኑ ነው ፤ ዶ/ር አብይም በቅርቡ...ላለፉት 150 ዓመታት ገዥ መደቦች የኦሮሞን ብሔር ሲያንቋስሹ የነበሩት በማንነቱ ላይ ተመስርተው ሳይሆን መሬቱን ፍለጋ ነበር... ማ   ታቸው ይታወሳል። ኦቦ ለማ መገርሳም ኢትዮጵያ ውስጥ የገዥ መደብ ጭቆና እንጂ የብሔር ለብሔር ጭቆና የለም ማለታቸው የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። በእኔ ዕይታ ይህ አስተሳሰብ መለስ ዜናዊ ይዞት ከተነሳው የብሔር ፖለቲካ እሳቤ የተለየ ነው፤ መለስ የአንድን ብሔር ገዥ መደብ ሳይሆን አጠቃላይ ብሔርን(የአማራን) እንደጠላት ቆጥሮ በማኒፌስቶው እስከማስፈር የዘለቀ ፖለቲከኛ ነው። አሁን እነ አቦ ሌንጮ፤ ኦቦ ዶ/ር አብይና ኦቦ ለማ መገርሳ የብሔር ፖለቲካውን የሊሕቃኑ ብቻ አድርገው የማስመራቸው ጉዳይ የለውጡ አካል ከሆነ እሰየው የሚያሰኝ ነው።

**2. ታሪክ ሌላ፤ ትርጉም ሌላ!**

ኦቦ ሌንጮ ሌላው የፈፀሙት ሕፀፅ ከታሪክ ትርጉም(Interpretation) ጋር የተያያዘ ነው። የ"Historicism" ዕሳቤ አቀንቃኞች ለአንድ ታሪካዊ ሁነት አያሌ ትርጉሞች ሊኖሩ እንደሚችሉ ይዘነጋሉ። ትርጉሙን የሚሰጠው ደግሞ አሁን ያለው ነባሩ ትውልድ እንደሆነም ጨርሰው ይረሱታል። ለምሳሌ ኦቦ ሌንጮ ከኢትዮጵያ ታሪክ አንጻር ወያኔ/ኢህአዴግን ያለፈውን ታሪክ ተቀባይ ብቻ አድርገው ስለውታል። የሚገርመው ግን ያለፈውን ታሪክ ተርጉሞ የራሱን አቅጣጫ የሚይዘው ደግሞ ወያኔ/ኢሕአዴግ ራሱ መሆኑ ነው። ስለዚህም ቀጣዩ ትውልድ ያለፈው ታሪክ ተቀባይ ብቻ አይደለም ፤ተርጓሚም ነው። ያለፈውን ታሪክ ብቻ በወሳኝነት አስቀምጦ "Historical determinist" መሆን ትልቅ ስህተት ነው። እኛም ሀገር ሕልም እንደፈቺው ነው ይባል የለ? ትናንት የተከሰተው ታሪክም አንድምታው እንደየተርጓሚው ይለያያል። ይህን አስመልክቶም ካርል ፖፐር በ" The Poverty of Historicism" መፅሐፉ ላይ እንደዚህ ይላል፦ "Historicism tends to mistake historical interpretations for theories. When studying history, we can only examine a limited aspect of the past. In other words, we must apply a historical interpretation, it is necessary to appreciate plurality of valid interpretations (although some may be more fertile than others)"

እንግዲህ "Hisotricism" አቅም-አልባ...በፖፐር አባባል ደግሞ ምስኪን ፍልስፍና...መሆኑ የሚረጋገጠው ትርጓሜው ዘንድ ሲመጣ ነው። ለአንድ ታሪካዊ ሁነት ከአንድ በላይ ትርጓሜዎች በሚኖሩበት ጊዜ እንደመነሻ መጠቀም ያለብን የትኛውን ይሆን? ለምሳሌ በአኖሌው የጡት ቆረጣ ውዝግብ ዙሪያ ብዙ ትርጉሞች ይሰጣሉ፤ከዚህም ባለፈ በኦሮሞ ታሪክ ዙሪያ የዶክተሬት ዲግሪያቸውን የሰሩ የኦሮሞው ምሁር ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ(በቅርቡ በሞት ተለይተውናል) የአኖሌ ሐውልት ትርክት ፈጽሞ በታሪክ ውስጥ ያልተመዘገበ ነው ብለው ሲከራከሩ፤ሌሎች ደግሞ ቆረጣው እውን ነው ከማለትም ባለፈ ሐውልት አስቁመውለታል። የትኛውን እንመን?  ስለዚህም ኦቦ ሌንጮ ለብሔር ፖለቲካው ወያኔ-ኢሕአዴግ መመስገንም መነቀፍም የለበትም ያሉት ፈጽሞ ከእውነታ የራቀ ነው፤ይህ ማጠቃለያቸው የታሪክ ተርጓሚውን ሚናን ሙሉ በሙሉ የዘነጋ ነው።

ከታሪክ አተረጓጓም ጋር በተያያዘ ኦቦ ሌንጮ አሁንም ሌላ ትልቅ ስሕተት ፈጽመዋል። በፅሑፋቸው የኢትዮጵያን የብሄር ፖለቲካን ምንጭ ለመተንተን የማርክስን አባባል መጠቀማቸው በራሱ ራስን በራስ እንደማጥፋት(suicide commitment) የሚቆጠር ነው..ያው በሬም የሚውለው ከአራጁ ጋር አይደል? ማለትም ካርል ማርክስ ለብሔር ፖለቲካ ጥብቅና በዋቢነት መቆም የሚችል ፈላስፋ አይደለም።  ኦቦ ሌንጮ ካርል ማርክስ አሁን በሕይወት ኖሮ የአቶ ሳሃሉን ንግግር ለማርክስ ቢያሳዩት ማርክስ የሚሰጠው ትርጉም ከኦቦ ሌንጮ ሙሉ በሙሉ የተለየ በሆነ ነበር፤ምክንያቱም ካርል ማርክስ ሁሉንም የታሪክ ፍሰቶችን የሚያየው በብሔር ፖለቲካ መነጽር ሳይሆን በመደብ ትግል መነፅር ነው። ለማርክስ ዋነኘውና የሁሉም ታሪካዊ ሁነቶች ምንጩ የኢኮኖሚ መደብ ነው፤ ማርክስ የብሔር ግጭቶችንም ጭምር የሚረዳው የመደብ ግጭቶች ነፀብራቅ እንደሆኑ(superstructure) ብቻ ነው።እናም በአጭሩ ካርል ማርክስ በሕይወት ቢኖር ወያኔ-ኢሕአዴግ የብሔር ፌዴራሊዝምን እንዲያወቅር ፈጽሞ አይመክራቸውም ነበር

ማለት ነው። ለብሔር የፖለቲካን ቅርጽ እየሰጠ ጭቁኑን ሕዝብ የሚበዘብዘውን ገዥውን መደብ ብቻ እንዲታገሉ ይመክራቸው ነበር። ለምሳሌ የሀገሪቱ ሀብት ስርጭት ሚዛኑ መዛነፍ ሲጀምር የተረሳው ሕዝብ ጥያቄውን ለማቅረብ በብሔር መደራጀት ይጀምራል፤በዚህ ወቅት ብሔር ለማርክስ የገዥው መደብ ኢ-ፍትሀዊነት መገለጫ ሆ ኖ ነው የሚቆጠረው! በእርግጥ ካርል ማርክስ ሁሉንም ታሪካዊ ሁነት ወደ መደብ ትግል መመንዘሩ የሚያስተቸው ቢሆንም ከብሔር ጋር በተያያዘ ግን አስተሳሰቡ ተቀባይነትን የሚያገኝበት አጋጣሚዎች አሉ። ለምሳሌ በሀገራችን እየተበራከተ የመጣው ሥራ-አጥነት ለብሔር ግጭቶች መስፋፋት እያበረከተ ያለው አስተዋጽዖ ቀላል አይደለም። ከዚህ በኋላም ሀገራችንን ሊያሳስበት የሚገባው የነዚህ ሥራ-አጥ ወጣቶች ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ነው። መንግስት ርብርብ አድርጎ የሥራ መስክ ካልፈጠረላቸው በብሔር ግጭቶች ዘርፍ ኢንቨስት ለማድረግ ያሰፈሰፉ አያሌ የውስጥም የሆነ የውጪ ኃይሎች በዝቅተኛ ወጪ መጠነ ሰፊ ሽብር ሊፈጥሩ ይችላሉ።

ለማጠቃለል ያህልም ኦቦ ሌንጮ ለታ በቅርቡ በለቀቁት ፅሑፍ ሁለት መሰረታዊ ስሕተቶችን ፈጽመዋል። የመጀመሪያው ያሰፈሩት የራሳቸውን ሐሳብ ብቻ መሆኑ ነው፤በዚያኛው ጎራ ያሉትን ተነፃፃሪ ንድፈ ሐሳቦችን ሆን ብለው ደብቀዋል፤ አሊያም የአንፃራዊ ፖለቲካ ዕውቀታቸው አጠያያቂ ነው፤ ምክንያቱም እሳቸው ያወደሱት የ"Historicism" ፍልስፍና በአንዳንድ የዘርፉ ምሁራን ውድቅ ከተደረገ 60 ዓመታት አልፈዋልና። በሁለተኛ ደረጃ ኦቦ ሌንጮ ለታ ለአንድ ታሪካዊ ሁነት አያሌ ተፎካካሪ ትርጓሜዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ያስተዋሉ አልመሰለኝም። የአቶ ሳሃሉ ፀዳሉ ንግግር ለኦቦ ሌንጮ ወደ ብሔር ትግል ጎዳና የሚወስድ ነው፤ ለካርል ማርክስ ግን ወደ መደብ ትግል የሚመራ ነው፤ እንደዚህ ዓይነት አሻሚ ትርጉሞች በታሪክ ዲስፒሊን ውስጥ የትየለሌ ናቸው። በአንፃሩም "Historicism" በአሻሚ ትርጉሞች መካከል ይዋልላል፤ባተሌ ምስኪን ይሆናል...ካርል ፖፐር በአጭር ቃል ከሽኖ አስቀምጦታል... "Historicism" ደሃ ነው፤ መናጢ ነው።

በመጨረሻም አንድ ነገር ልበል፦ ቋንቋንና ብሔርን መሠረት አድርጎ ለአባል የክልል መንግስታት እስከወዲያኛው የመገንጠልን መብት የሰጠው ፀጉረ ልውጡ የወያኔ-ኢሕአዴግ ፌዴራሊዝም በንድፈ ሐሳብም በተግባርም ላለፉት 28 ዓመታት ተሞክሮ የከሸፈ አካሄድ ነው። አንድ ፖለቲካዊ መስመር በአንድ ሀገር ላይ ለ28 ዓመታት ያህል ተሞክሮ ውጤቱ ዕልቂትና በገዛ ሀገር እንደ ስደተኛ መፈናቀል ከሆነ ኢሕአዴጋዊያን ወደ ልቦናቸው ተመልሰው ቆም ብለው ቢያስቡበት መልካም ነው። በእርግጥ በአንድ ነገር አምናለሁ፤ ወያኔ በማዳበርያ ጭምር የዘራውን የብሔር ፖለቲካን በአንድ ጀምበር መንቀል አይቻልም፤ ስለዚህም ከሁሉም በፊት ኢሕአዴግ በብሔር ፌዴራሊዝም ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ "አልደራደርም" የሚለውን ግትር አቋሙን ያለዝብ፤ ቀጥሎም በብሔር ፅንሰ ሐሳብ ምንነት ዙሪያ ሰፋፊ ውይይቶች ይደረጉ። ሌላው ቀርቶ ኢሕአዴግ በብሔር ፅንሰ ሐሳብ ዙሪያ ያለውን ግንዛቤ ከዘርፉ ሳይንስና በሶሻል አንትሮፖሎጂስቶች በገሃዱ ዓለም ከተደረጉ ጥናቶች(empirical studies) ጋር ማስታረቅ ከቻለ ዕድለኞች ነን። ተሳክቶልን የወያኔ-አሕአዴግ ስሁት አስተሳሰቡ ከተለወጠ ቀጣዩን አብረን የምናየው ይሆናል። የሰው ልጆችን መብት በማክበር ውስጥ የብሔር መብቶችን ጨምሮ ሌሎቹንም መብቶች ማክበር ያን ያህል አዳጋች መስሎ አይታየኝም...ፍቅሩ መተሳሰቡ አብሮነቱና የዘመናት ታሪካዊ ትስስሮሹ ከጠነከረ ማለቴ ነው ።

አመሰግናለሁ።